የሰበር መ/ቁ. 18780

ቀን ግንቦት 07/1998 ዓ.ም.

**ዳኞች:-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ጌታቸው ምህረቱ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

**አመልካች:-** የኢት/ ንግድ ባንክ

**ተጠሪ:-** ወ/ሮ ከበቡሽ ጉልላት

## ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ/ን/ ይወሰንልኝ/ን/ የሚል ዳኝነት በመጠየቅ የሚቀርብ ክስ የክስ ምክንያት /Cause of action/ አለው? ወይስ የለውም? ጉዳዩንስ ለመዳኘት የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን አለው? ወይስ የለውም? የሚለውን የህግ ነጥብ የሚመለከት ነው።

የም/ኦሮሚያ አሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ተጠሪ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ/ን/ ይወሰንልኝ/ን/ በማለት ያቀረቡትን ክስ በመቀበል አከራክሮ ውሣኔ ሰጥቷል። በውሣኔው ላይ ይግባኝ የቀረበለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ከላይ የተመለከተውን የህግ ነጥብ ሳይመረመር አልፎታል።

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክል ግልባጭ
ፊርማ [signature] ቀን 15/9/98

አመልካች በዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ተጠሪ/ዎች ቀርበው የፅሑፊ መልስ አቅርበዋል፡፡

ችሎቱም ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ/ን/ ይወሰንልኝ/ን/ የሚል ዳኝነት በመጠየቅ የሚቀርብ ክስ የክስ ምክንያት /cause of action/ አለው? ወይስ የለውም? የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን አለው? ወይስ የለውም? የሚለውን የህግ ነጥብ መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ መርምሯል፡፡

ይህ ችሎት በመ.ቁ. 16273 ጥቅምት 22 ቀን 1998 በሰጠው ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የህጉን ድንጋጌዎች በመተርጎም አንድ ሠራተኛ ከውሉና ከአሰሪና ሠራተኛ ሕጉ አንፃር ሊያገኘው የሚገባና የቀረበት ጥቅም ካለ የቀረበት ጥቅም እንዲሰጠው መጠየቅ /ክስ ማቅረብ/ የሚችል ሲሆን ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ ይወሰንልኝ በሚል ብቻ የሚቀርብን ክስ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድም ሆነ የሥራ ክርክር ችሎት ተቀብለው ሊያዩ የሚችሉበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በሌላም በኩል ቢሆን በመ/ቁ. 18180 አግባብነት ያላቸው የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ድንጋጌዎችን በመተርጎም የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የማየት ስልጣን የተሰጠው የወል የሥራ ጉዳዮችን ነው፡፡ አንድ የሥራ ክርክር የወል የሥራ ክርክር ነው የሚባለው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡ በአንፃሩ አንድ የሥራ ክርክር የወል ሳይሆን የግል የሥራ ክርክር ጉዳይ ነው የሚባለው የክርክሩ ውጤት

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለ ግልባጭ
ፊርማ [signature] ቀን 15/9/98

በተከራከረው ሠራተኛ /ሠራተኞች/ ላይ ብቻ ተወስና የሚቀር ሲገኝ ነው በማለት የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በዚህ ጉዳይም የም/ኦሮሚያ አሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ተጠሪዎች ያቀረቡት ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ/ን/ ይወስንልኝ/ን/ በማለት ያቀረቡትን ክስ የክስ ምክንያት የሌለው ከመሆኑም በአሻገር የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት የሚያስከትል ባለመሆኑ የወል የሥራ ክርክር አይደለም፡፡ በመሆኑም በሁለቱም ምክንያቶች የቀረበውን ክስ ውድቅ ማድረግ ሲገባው ጉዳዩን አከራክሮ በመወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ፈጽሟል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

- የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመ/ቁ. 517/01/97 በታህሣስ 19 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 21525 በየካቲት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
- ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ይ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለ ግልባጭ
ፊርማ [signature] ቀን 15/9/98